የዚህ ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 43912

ሰኔ 15 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** አፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ - ጠበቃ ረዳኢ ባራኺ ቀረበ

**ተጠሪዎች፡-** 1. የአቶ ኢብራሂም ሙሣየ- ወራሾች በሌሉበት

2. ሰይድ ኢብራሂም - በሌለበት

መዝገቡን መረምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ በመኪና ላይ ደረሰ የተባለውን ጉዳት መሰረት በማድረግ የቀረበ የካሣ ክፍያ ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ከሣሽ የነበረው አመልካች ነው፡፡ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሰረተው የመድን ዋስትና የገባለት የደንበኛው መኪና በሁለተኛ ተጠሪ ሾፌርነት ሲሽከረከር በነበረው በአንደኛ ተጠሪዎች መኪና ተገጭቶ ጉዳት ስለደረሰበትና በዚህ ምክንያትም መኪናውን ለማስጠገን ወጪ በማድረጉ ይህንኑ እንዲተኩለት ነው፡፡ በአንደኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች በተደረገላቸው ጥሪ መሰረት ባለመቅረባቸው ክርክሩ በሌሉበት የተሰማ ሲሆን፣ሁለተኛ ተጠሪ ግን ቀርቦ መልሱን እንደሰጠ ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ክሱን የሰማው ፍ/ቤትም ከሁለቱ ወገኖች የቀረበለትን ክርክር ከመረመረ በኋላ፣ሁለተኛ ተጠሪን ከክሱ ነፃ በማድረግ በአንደኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች ብር 22,387.79(ሃያ ሁለት ሺህ ሦስት መቶ ሰማኒያ ሰባት ብር ከሰባ ዘጠኝ ሣንቲም) ከነወለዱ እንዲከፍሉ ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች በውሳኔው ስላልተስማማ ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ የነበረ ሲሆን፣ፍ/ቤቱ ክሱ የቀረበው የግዛት ሥልጣን ለሌለው ፍ/ቤት ነው የሚል ምክንያት በመስጠት ይግባኙን ካለመቀበሉም በላይ፣በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔም ሽሮታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች በሥር ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታውን አቅርቦአል፡፡ እኛም አቤቱታውን መሰረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ተጠሪዎች በተደረገላቸው ጥሪ መሰረት ባለመቅረባቸው ክርክሩ የተሰማው በሌሉበት ነው፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የግዛት ሥልጣንን መሰረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን የተመለከተው ክሱን የሰማው ፍ/ቤት የግዛት የዳኝነት ሥልጣን ነበረው ወይስ አልነበረውም? የሚለው ጭብጥ አንፃር ነው፡፡ ለሰጠው ውሳኔ በዋቢነት የጠቀሰውም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሥሕ/ቁ. 27/1/ የተመለከተው ድንጋጌ ነው፡፡ ፍ/ቤቱ ይህን ድንጋጌ ለመጥቀስ የበቃው የክሱ መነሻ በሚንቀሳቀስ ንብረት የደረሰ ጉዳት ነው የሚል ምክንያት በመያዝ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይሁንና በተያዘው ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ድንጋጌ በቁጥር 27/1/ የተመለከተው ሳይሆን፣በቁጥር 24/3/ የተመለከተው እንደሆነ ነው በበኩላችን ለመገንዘብ የቻልነው፡፡ አመልካች በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ የንግድ ማህበር እንደመሆኑ ጉዳዩ በፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5(6) መሰረት በፌዴራል ፍ/ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚወድቅ ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 24/3/ በግልጽ እንደተቀመጠው በኢንሹራንስ ውል አፈፃፀም ምክንያት ክርክር የተነሳ እንደሆነ ክሱ የኢንሹራንሱ ኩባንያ ዋና መሥሪያ ቤት በሚገኝበት ቦታ ባስቻለው ባለሥልጣን ፍ/ቤት ሊቀርብ ይችላል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች የኢንሹራንስ ኩባንያ ነው፡፡ ዋና መሥሪያ ቤቱ በዚህ በአዲስ አበባ ስለመሆኑም ይታወቃል፡፡ ክሱም የቀረበው በዚህ በአዲስ አበባ ላስቻለው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ በጉዳዩ ላይ የግዛት ክልል የዳኝነት ሥልጣን የለውም የሚባልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ያየው የተሳሳተ ወይም ለጉዳዩ ተገቢነት የሌለውን ሕግ መሰረት በማድረግ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 48183 ኅዳር 24 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሮአል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተከፈተው የይግባኝ መዝገብ ጉዳዩን እንዲቀጥል በማድረግ እና ወደ ጉዳዩ ሥረ ነገር በመግባት ክርክሩን ሰምቶ ተገቢው ውሳኔ ይሰጥ ዘንድ ይመለስለት ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር አመልካች ወጪና ኪሣራውን ራሱ ይቻል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ